


# ለጌታ መመለስ ተዘጋጁ!

በ ***በርናርዳ ፈርናንዴዝ***
www.DivineRevelations.info/BERNADA

እህት በርናርዳ ፈርናንዴዝ በ2 ጉዞዎች ከኢየሱስ ጋር ወደ ሰማይና ወደ ሲኦል ተወስዳለች። ለጌታ ቅዱሳን የተዘጋጁ የሰማይ ብድራቶችን፣ ንጥቀትቅን፣ ታላቁን ግብዣ እና የሕይወትን ዘውዶች እንድታይ ተደርጋለች። እርሷም የቤተክርስቲያንን ሁኔታ፣ የሚመጡትን ፍርዶች፣ በሲኦል ውስጥ የጠፉትን ነፍሳት አይታለች።

## የመጀመሪያ ጉዞዬ

በዚያ ማለዳ ደህና እየተሰማኝ አልነበረም ፥ ባለቤቴ እኔን ትቶ ወደ ሥራ መሄድን እምቢ አለ። ብቻዬን እንዳልሆንሁ ነገርሁት። እርሱ ከሄደ በኋላ ፥ እየሞትሁ እንደሆነ ተሰማኝ። ስለዚህ ለአንዳንድ ጓደኞቼን፣ እና ለእንጀራ እናቴ ለመደወል ወሰንሁ። የእንጀራ እናቴ እንዲህ በማለት መለሰች: "በርናርዳ፥ እግዚአብሔር ዛሬ ይባርክሻል ፥ አትፍሪ።" ይኸው መልስ ከደውልሁለት በክርስቶስ ከሆነ ከሌላ ወንድም መጣ፥ ነገር ግን እርሱ እንዲህ በማለት ጨመረ: "በርናርዳ ከአልጋሽ ተነሺና እግዚአብሔርን አመስግኚ፣ ወደ እርሱ ጩኺ እና እርሱን አክብሪው።"

ጥንካሬ በማጣቴ ሳልጠቃ፥ እንዲህ እያልሁ ወደ ጌታ ጮኽኩ: "*ጌታ ሆይ አንተ ብርታቴ ነህ፥ ና እና እርዳኝ።*" ለመቆም ሞከርሁ፥ ነገር ግን ጥንካሬዬ ትቶኛል። ድምፄ ከዚህ በኋላ ሊሰማ አልቻለም፥ ነገር ግን እየሞትኩ እንዳለሁ ስለተሰማኝ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ ወደ እግዚአብሔር በነፍሴ እየጮህኩኝ ነበር። በድንገት ክፍሌ እሳት በሚመስል ብርሃን በራ። ወዲያውኑ ፍርሃቴ ጠፋ እኔም መላእክት ወደታች ሲወርዱና በክፍሌ ውስጥ ሲራመዱ አየሁ። እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ በግልፅ መስማት ችዬ ነበረ። በድንገት እጅግ ግሩም አስደናቂ ሕያው ነገር መጥቶ ታየ፥ ከማንኛውም መልአክ እጅግ የላቀ ግሩም ድንቅ። እርሱ በትከሻው ወደታች የሚወርድ ወርቃማ ድግ ባለው ነጭ ልብስ ተላብሶ ነበር። በደረቱ ላይ በወርቅ: "**ታማኝ እና እውነተኛ**።" የሚል ተጽፎአል። *የእርሱ ፊት* ገርነት(ቸርነት) እና ፍቅር እያሳየ ነበር። የነገሥታት *ንጉሥ* እና የጌታዎች *ጌታ መሢሑ*(ክርስቶስ) ኢየሱስ ከፊት ለፊቴ ነበረ። ስሙ የተባረከ ይሁን!


ኢየሱስ ቀረበኝ፥ ራሴን ነካና ይህን ነገረኝ: "***እኔ ለአንቺ የምትሁት ኢየሱስ ነኝ። በእጆቼ ያሉትን እኚህን (የችንካር) ምልክቶች ተመልከቺ፥ እኚህ እስከአሁን ለአንቺ እዛ(በቦታቸው) አሉ። እኔ ላናግርሽ ከክብር ዙፋኔ ላይ ወደታች መጥቻለሁ፤ በህይወትሽ ውስጥ ትክክል መሆን(መስተካከል) ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አንቺ ሰነፍ እና ቶሎ የምትበሳጪ ነሽ። ከዚህም በላይ፥ 25% ወይም 95% ክርስቲያን አልፈልግም፥ ነገር ግን 100% ክርስቲያን(የሆነ) እፈልጋለሁ። ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ ከፈለግሽ፥ እኔ ራሴ ቅዱስ እንደሆንሁ አንቺም ቅዱስ መሆን አለብሽ፤ አንድ ጉዞ ልወስድሽ መጥቼአለሁ።***"




"ጌታ ሆይ፥ የሚሲዮናዊ(የወንጌል ስብከት) ጉዞ ነው?" ብዬ ጠየቅሁት። "***አይደለም።***" በማለት መለሰ። ከዛ በእጆቼ ይዞ ወደላይ አነሣኝ፥ እና በየዋህነትና በፍቅር አናገረኝ። እስከ መስኮቶቹ ድረስ አመጣኝ፥ የኒው ዮርክን ከተማ ተመለከተ። በፊቱ ላይ ኀዘን አየሁ። እርሱ አነባና እንዲህ አለ: "***የእኔ ቃል ደህና ተደርጎ ጥሩ ተሰብኮአል፥ ነገር ግን ሰዎች አያዳምጡም። የዚህች ከተማ ኃጢአት አባቴ ጋር ደርሶአል።***"

ከተማዋ በግብረሰዶማውያን ተሞልታለች፤ ከእነርሱ መካከል የፖለቲካ ሰዎች ነበሩ። ጌታ: "***ይህች ሌላ ሰዶም ናት፥ እኔ ግን ሕያው ነኝ የአባቴም ፍርዶች በዚህች ከተማ ላይ ፈጥነው ይወርዳሉ።***" ብሎ ነገረኝ። ከዚያም እኔ እያለቀስሁ በጌታ ፊት ተንበረከክሁ እርሱም ይህን ነገረኝ: "***አትፍሪ። ፍርድ በዚህ ዓለም ላይ ሲወርድ፥ ቤተክርስቲያኔ በምድር ላይ አትሆንም።***"

እርሱ ከዚያ በድጋሜ ወደ አልጋዬ መራኝ ከቤተክርስቲያኔም(ከሆነ) ለአንድ ወንድም እንድደውል ጠየቀኝ። መንፈሴ ከአካሌ እንደምትወጣ፣ እነርሱም አስከሬኔን ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ ማንኛውም የቀብር ስነ-ሥርዓት እንዳያመጡት እንድነግረው ጠየቀኝ። በዚያ ፈንታ፥ ትንሣኤና ሕይወት የሆነውን እንዲታመን ለባለቤቴ መንገር እንዳለባቸው። (ዮሐንስ 11: 25) ጌታ በድጋሜ: "***ሕይወት የምሰጥ እኔ፥ መንፈስሽን ወሰድሁ፥ ነገር ግን አንቺ ተመልሰሽ ትመጪና ሰዎች እኔን ሙሉ በሙሉ እንዲታመኑኝ ለሰዎች ትነግሪአቸዋለሽ። የሚያምንብኝም በፍጹም አይሞትም።***" (ዮሐንስ 11:26) ብሎ ነገረኝ። እርሱ እጆቹን ዘረጋ እኔም መንፈሳዊ አካል ከሥጋዊ አካሌ ሲወጣ አየሁ። ነጭ ለብሼ ነበር እኔም እንደ ጌታ እያበራሁ ነበረ፥ እርሱ ይህን ነገረኝ: "***ተመልከቺ! የእኔን ቃል የሚታዘዙ ክርስቲያኖች በቅርቡ የሚኖራቸው አካል ይህ ነው።***"



አሁን በግድግዳዎች ውስጥ መሄድ እንደምችል ተገነዘብሁ። በእጄ ይዞኝ የነበረው ጌታ "***ተመልከቺ***"! አለ። ስዞር፥ አካሌ(ሥጋዬ) ያለመንፈስ ሆኖ አየሁት። ሥጋዊ አካሌ ጥቅም የሌለው (ዋጋ ቢስ) እንደነበረ፥ አቧራ ብቻ እንደሆነ፥ እንደማንኛውም ሥጋዊ አካል በሞት ጊዜ በድጋሜ አቧራ እንደሚሆን ገለጸልኝ። እኔ የነበረኝ አዲሱ አካል እርሱ (የነገሥታት ንጉሥ የጌታዎች ጌታ አምላካችን የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ) ለሰው የሰጠው እጅግ የከበረው መንፈስ( the spirit) እንደሆነ ጨምሮ ተናገረ። ቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይመራኛል ብዬ አስቤ ነበር፥ ነገር ግን ጉዳዩ ይህ አልነበረም።



ከምድር በታች በመሿለኪያ ዋሻ ውስጥ ወደ ታች ወረድን፥ የሆነ ቦታ እየቀረብን ሳለ ሊታገሱት የማይቻል ሽታ እንዳለ መገንዘብ ቻልሁ። "*ጌታ ሆይ ወደዚያ ቦታ ውስጥ መሄድ አልፈልግም።*" አልሁ። እኛ ግን ሄደን ገባን፤ ያ ቦታ እጅግ ጨለማ ነበር። ሰዎች ሲሠቃዩ፣ ሲያነቡና ሲጮኹ ሰማሁ። የመሿለኪያው ዋሻ መጨረሻ ላይ ስንደርስ፥ አንድ አለት ላይ ተቀመጥን ጌታም: "***ተመልከቺ***"! በማለት ነገረኝ። ሰዎች ሲሠቃዩ አየሁ። በሲኦል፥ ሰዎች እያለቀሱ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፥ ማንም ስለሌሎች አያስብም(አይጠነቀቅም)።

ውድ ወንድሞች እና እህቶች፥ **ሲኦል እውን እንደሆነ** ተገንዝቤአለሁ። አነባሁ እና አነባሁ፥ ጌታን ስመለከት፥ እርሱ: "***ያየሽውን ጠብቂ፥ አትርሺውም።***" በማለት ነገረኝ። ሰዎቹ "*አውች! አውች! ይህ ለዘላለም ነው! ይህ ለዘላለም ነው! ሥቃይና ጥላቻ ከዘላለም እስከዘላለም።*" በማለት እየጮኹ ነበር።

ወደ ጌታ ዞርሁና “*ከቤተሰቤ በሲኦል ውስጥ አለ?*” በማለት ጠየቅሁት። **እርሱ** “***የቤተሰብሽን አባል እንድታዪ አልፈቅድልሽም።***” በማለት መለሰልኝ። ስለዚህ “*እኔ የማውቀው እዚህ አለ?*” ብዬ ጠየቅሁት። “***አዎን እኔም እንድታዪው እፈቅድልሻለሁ።***” በድንገት አንድ ወጣት ሰው ከሲኦል ጥልቆች ውስጥ ሲመጣ አየሁ: አሌክሳንደር ነበር።

ይህን ወጣት ሰው ባለቤቴ እና እኔ ዶሚኒካ ሪፐብሊክ ውስጥ በተካፈልንበት በአንድ ክሩሴድ ላይ አውቀዋለሁ። በክሩሴዱ ጊዜ፥ አንድ ***ድምፅ*** “***ተነሺ፥ በዚህ እያለፈ ያለውን አሌክሳንደርን ተገናኚው። እኔ የመጨረሻ እድል እየሰጠሁት ነውና፥ ይህን መልእክት እንዳይጥል(ሳይቀበል እንዳይቀር) ንገሪው።***” ሲለኝ ሰማሁ። በዛን ሰዓት ***ጌታ***ን ባላየውም እንኳን፥ ይህ ድምፅ ***የጌታ ድምፅ*** ነበረ። ***ጌታ*** የነገረኝን ለአሌክሳንደር ነገርሁት፥ እንዲህ ነበረ እርሱ ምላሽ የሰጠው: “እናንተ ክርስቲያኖች ሁላችሁም ሞኞች ናችሁ። **ኢየሱስ ክርስቶስ** እየመጣ እንደሆነ ለሰዎች በመንገር ሰዎችን ታታልላላችሁ፥ እኔ አሌክሳንደር፥ ይህ እውነት ነው ብዬ አላምንም።” እኔ: “*አሌክሳንደር ሆይ፥ **እግዚአብሔር** ሕይወትን ይሰጣል ሲፈልግም ይወስዳል፤ አሌክሳንደር፥ አንተ በቅርቡ ትሞታለህ።*” ብዬ ነገርሁት። እርሱ: “እኔ ለመሞት በጣም ወጣት ነኝ፥ እኔ በዚህ ምድር ላይ ብዙ መልካም የጨዋታ(የቀልድ) ዓመታት አሉኝ።” በማለት መለሰ።



ያ በእውነት ለአሌክሳንደር የመጨረሻ እድል ነበረ። ከሦስት ሳምንታት በኋላ፥ አሌክሳንደር ሰክሮ ሳለ ሞተ። የእርሱ መዳረሻ እርሱን ባየሁበት (በሲኦል) ይህ የሥቃይ ቦታ ነበረ። ሰካራም የ**እግዚአብሔር**ን መንግሥት እንደማይወርስ መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይጠቅሳል(ይናገራል)። (**ገላትያ 5: 21**)

በሲኦል ውስጥ ሰዎችን ስመለከት፥ አሌክሳንደር በሁለት ትልልቅ ትሎች ሲጠቃ(ጥቃት ሲደርስበት) አየሁ። “*አውች! አውች! አውች!*” እያለ እየጮኸ ነበር። እርሱ እየተሠቃየ ነበረ። እርሱ ለይቶ አወቀኝና ይህን ነገረኝ: “*እኔ የመጨረሻ እድሌን ችላ ብዬአለሁ። እኔ ዛሬ እየተሠቃየሁ እዚህ ነኝ። እባክሽ፥ ወደ መሬት(ምድር) ስትመለሺ፥ ቤተሰቦቼ ወደዚህ የሥቃይ ቦታ እንዳይመጡ ወደቤቴ ሂጂና **በኢየሱስ ክርስቶስ** እንዲያምኑና **የእርሱን ቃል** እንዲታዘዙ ለቤተሰቦቼ ንገሪአቸው።*”

ከዚያ ጌታ በሲኦል ውስጥ እየተሠቃዩ ያሉ ሺሆች ሰዎችን አሳየኝ፥ እና እንዲህ አለ፥ “***አየሽ፥ አንዳንዶቹ እነዚህ ሰዎች በምድር ላይ ሳሉ ያውቁኝ ነበር። አሁንም በምድር ላይ የት እንደሚሄዱ ሳያውቁ በመንገድ(በጎዳና) ላይ የሚሄዱ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ። ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደው መንገድ በጣም ጠባብ እንደሆነ እወቁ፥ በድጋሜ የበለጠ ይጠብባል። እናንተ እንደ ወርቅ ንጹህ ትሆኑ ዘንድ በምድር ላይ ችግሮች ይኖራሉ፥ ነገር ግን እኔ እንደ ኃያል ተዋጊ ከፊታችሁ ነኝና አትፍሩ።***”

“*በዚህ ሲኦል ውስጥ ክርስቲያኖች አሉ?*” በማለት ጠየቅሁት። **እርሱም** መለሰ: “***አዎን፥ ለምን እንደሆነ ታውቂአለሽ? በእኔ ያምናሉ ነገር ግን እንደ ቃሌ አልተራመዱም(አልኖሩም፥ አልሄዱም)። ከእነዛ ክርስቲያኖች ብዙዎቹ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሆኑ፣ ከእረኞቻቸው(ከፓስተሮቻቸው፥ ከካህናቶቻቸው) እና ከቤተሰባቸው ፊት ሲሆኑ ብቻ መልካም ምግባር የሚፈጽሙ አሉ። ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን በጣም እያታለሉ ናቸው። የአባቴ ዓይኖች ሁሉንም ያያሉ እርሱም(እግዚአብሔር አብ) የትም ሆናችሁ የት እያንዳንዱን ቃል ይረዳል። በአባቴ ፊት፣ በዲያብሎስ ፊት እና በዓለም ፊት ቅዱስ ህይወት የሚኖሩበት ሰዓቱ አሁን እንደሆነ ለሕዝቤ ንገሪ። ዲያብሎስ ሕዝቤን የምከሰስበት ምንም መብት አይኑረው፤ ዓለምም አንድም ጣት ሕዝቤ ላይ አይጠቁም።***” (**1ኛ ጴጥሮስ 1: 14-16**)



ከዛ ወደ እሳት ባሕር ሄድን። የእሳት ባሕሩም በጣም በመጥፎ ሁኔታ ይሸታል፥ ጌታም እንዲህ አለ፥ “እዚያ የምታዩው ለዲያብሎስ፣ ለሐሰተኛው ነቢይ፣ እና ለክርስቶስ ተቃዋሚ የተዘጋጀው የእሳት ባሕር ነው። ይህን ቦታ ለሰዎች አላዘጋጀሁትም፥ ነገር ግን እኔን እንደ አዳኛቸው የማያምኑብኝ ሁሉ እና እንደ ቃሌ የማይኖሩ ሁሉ እዚያ ይሄዳሉ” (ራእይ 20:14)

በዛ ጊዜ ኢየሱስ ሲያነባ አየሁ እርሱም በድጋሜ ነገረኝ: “ወደ መንግሥተ ሰማይ ከሄዱት ይልቅ የጠፉት በጣም ብዙ ናቸው።” በእያንዳንዱ ደቂቃ እየሞቱ የነበሩትን ቁጥር(ብዛት) አሳየኝና እንዲህ አለ፥ “ተመልከቺ! የጠፉት ምን ያህል ናቸው! ቤተክርስቲያኔ የእኔን ኃይል መቀበሏ ምንም እንኳ እውነት ቢሆንም እርሷ ግን ተኝታለች፤ እርሷ የእኔ ቃል እና መንፈስ ቅዱስ አላት፥ እርሷ ግን ተኝታለች። ሲኦል እንደሌለ የሚሰብኩ ሰዎች በምድር ላይ አሉ። ሂጂ እና ይህ ቦታ እውን እንደሆነ ንገሪያቸው።”

እጅግ ኃይለኛው እሳት ይሰማኝ ነበር። ያን ቦታ ትተን ወጣን እና ወደ መንግሥተ ሰማይ ሄድን። እስከ ሁለተኛው ሰማይ ወደ ላይ ወደ ላይ መሄዳችንን ቀጠልን። እርሱም ፀሐይንና ከዋክብትን አሳየኝና፥ “እነዚህን ከዋክብት ተመልከቺ፥ እኔ እያንዳንዳቸውን በስም እጠራቸዋለሁ። ይህን ፀሐይ አየሽው፥ በእኔ ኃይል ነው በጻድቃንም በክፉዎችም ላይ የሚያበራው። ነገር ግን ፀሐይ የማያበራበት ቀን ይመጣል፥ ሁሉም ጨለማ ይሆናል።” አለ። (የሐዋርያት ሥራ 2:20)



ከዚያም በይበልጥ ወደላይ ወጣን የእግዚአብሔርም መንግሥት ደረስን። ውብ ቤቶችን አየሁ። የእነዚያ ቤቶች ግድግዳዎች በጣም ከፍተኛ(ከፍ ያሉ)፣ ከንጹሕ ወርቅና ከከበሩ ድንጋዮች የተሠሩ ነበሩ። እዚያ ከዕንቁ የተሠሩ አስራ ሁለት ደጆች ነበሩ፥ በደጆቹ ላይም አስራ ሁለት መላእክት ነበሩ። ወደ ውስጥ መግባት እንደምችል አላወቅሁም ነበር፥ ጌታ ግን ተመለከተኝና “ወደ ውስጥ መግባት ትፈልጊያለሽ?” አለ። “አሀ አዎን ጌታ ሆይ! የእውነት እፈልጋለሁ።” “እኔ ራሴ በሩ ነኝና ግቢ” (ወንጌለ ዮሐንስ 10:9)።

በዛ ቅጽበት በከበረው ደጅ ወደ ውስጥ ገባሁ እጅግ የሚያስደንቁ ውብ አበባዎች ያሉትን መናፈሻም አየሁ። “መናፈሻው ውስጥ መግባት ትፈልጊያለሽ? እኔ ይህን ለአንቺና ለሕዝቤ አዘጋጅቼአለሁና ግቢ።” ስገባ፥ አንዳንዶቹን አበባዎች በአንደላይ እያደረግሁ በቡድኖች መሰብሰብ ጀመርሁ። በመናፈሻው ውስጥ እንደ ሕፃን ልጅ ሮጥሁ። የያዝኳቸው አበባዎች እጅግ በጣም ጥሩ መአዛና ብዙ ቀለሞች ነበሯቸው። ጌታ አንድን(መልአክ) ጠራ። ልገልጸው የማልችለው ጠንካራና በጣም ውብ መልአክ ነበር። “ይህን ታዩአለሽ፥ እርሱ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ነው፥ የእኔን ሠራዊት የሚመራው እርሱ ነው። በድጋሜ ተመልከቺ!” ብሎ ጌታ ነገረኝ። እጅግ ኃያል ሠራዊት በፈረሶች ላይ ሆነው አየሁ ጌታም: “ይህ ሰው የሆነ ሠራዊት አይደለም፥ ነገር ግን የአባቴ ሠራዊት ነው። ይህ ሠራዊት የእውነት ዳግም ለተወለዱ ክርስቲያኖች የሚሰለፍ ነው፤ አትፍሪ፥ በዓለም ካለው ይልቅ የበለጠ ኃይለኛ ነው።” በማለት ነገረኝ።


ከዛ እርሱ ሌላ መልአክ አሳየኝ። “ይኸኛው ቃሌን ለሚታዘዙ ክርስቲያኖች መልእክተኛ ነው።” ያን በመስማቴ ደስተኛ ነበርሁ። ኢየሱስ(ያሑሹዋ) ይህን ነገረኝ: “ትኩረት የምትሰጪ ትጉሕ ልባም ሁኚ! እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የሙሴ አምላክ፣ የኤልያስ አምላክ ነኝ፥ እሳት ከሰማይ እንዲወርድ ያደረግሁ ነኝ፤ እኔ አልተቀየርሁም። በእነዚህ የመጨረሻው ዘመኖች እየኖሩ ያሉት ሕዝቤ እነርሱ የተዉትን ሁኔታ ላሳይሽ ነው።”



ደክመውና ታክተው(ተሰላችተው) የነበሩና ክርስቲያኖችን አየሁ። ጌታ ይህን ጥያቄ ጠየቀኝ: "ይህችን ቤተክርስቲያን በአሁን ሁኔታዋ ልወስድ እንደምችል ታምኚአለሽ? " ከዚያ እርሱ ይህን ነገረኝ፥ "ከእኔ ጋር የምወስዳቸው ክርስቲያኖች የከበሩ፣ ድል ነሺዎች፣ እንከን የሌለባቸው፣ ነቀፋ የሌለባቸው ይሆናሉ(ናቸው)። በሕዝቤ መካከል ውሸቶች፣ የፍቅር ማጣት አሉ፥ ሕዝቤ ተከፋፍሎአል። በእነዚህ የመጨረሻ ቀኖች ያሉትን የክርስቲያኖች ሁኔታ አሳየሁሽ፤ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደኖረች አሁን ላሳይሽ ነው። እነዛ ወንድሞችና እህቶች በእግዚአብሔር ክብር ተሞልተው ነበረ። እነርሱ በየጊዜው(ሳያቋርጡ) ጾሙና ጸለዩ፤ እነርሱ ቃሌን ያለምንም ፍርሃት ሰበኩ። የአሁኖቹ ክርስቲያኖች ግን እኔ እንደተቀየርኩ ያስባሉ፥ በተጨማሪም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እንደተቀየረ ያስባሉ። ዛሬ የክርስቲያኖች ትልቁ ስህተት በሰዎች የታቀደ የተደጋገመ ልማዳዊ( routine) ህይወት የመኖራቸው እውነታ ነው። ስለዚህ መልእክቶቹ ከመንፈስ ቅዱስና ከላይ እንደሆኑ ረስተዋል። ለባሪያዎቼ ለፓስተሮች(ለእረኞች) እነዚያን የተደጋገሙ ልማዳዊ ጉባኤዎች(ፕሮግራሞች) የሚተዉበት ሰዓት እንደመጣ ንገሪያቸው። ይህን ካደረጉ፥ የእግዚአብሔር ኃይልን በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ተገልጦ የነበረውን መንፈስ ቅዱስ በመሐከላቸው ታዩአለሽ። እርሱ ሙታን እንዲነሡ በማድረግ ኢጅግ በብዛት ምልክቶችን፣ ተአምራትንና ድንቆችን ያደርጋል (ያከናውናል)። መንፈስ ቅዱስ አሁንም ያው ነው፥ የተቀየራችሁት(የተለወጣችሁት) እናንተ ናችሁ። "



ክርስቲያኖች፥ ወደ መጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ሕይወት ተመልሳችሁ የምትመጡበት ሰዓቱ አሁን(አሁኑኑ) ነው። ከዚያ ይህን ውብ መናፈሻ ተውሁና ከወርቅ ወደተሠራው ተወዳጅ መንገድ(ጎዳና) ሄድሁ ጌታም እንዲህ አለ "ንኪ! አዎን ንጹሕ ወርቅ ነው። ኢጅግ በቅርቡ፥ ሕይወትን የሚሰጠውን እርሱን እጁን ይዘው በእነዚህ የወርቅ ጎዳናዎች ላይ ሊራመዱ እንደሆነ ሂጂና ለልጆቼ ንገሪያቸው። " (ራእይ 21:10-15)




ኦህ! በእነዚያ የወርቅ ጎዳናዎች ላይ መጓዝ እንዴት በጣም ጥሩ ነው! ከዚያ በኋላ በመላእክት፣ በሊቀ መላእክት እና በሱራፌሎች የተከበበ እጅግ አስደናቂ ግሩም ዙፋን አየሁ። በዙፋኑ ላይ የነበረውን እግዚአብሔርን "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ ሰማይና ምድር በክብሩ ተሞልተዋል። አሜን!" እያሉ ያለመቋረጥ እግዚአብሔርን እያወደሱ ነበር። "ቅዱስ ኢጆች ወደላይ ወደ እኔ ተነሥተው እኔ የምወደስበት ሰዓት መጥቶአል።"

የሕይወት ውኃ ወንዝ ከዙፋኑ ሲፈስስ አየሁ። ደግሞም የሕይወትን ዛፍ አየሁ በሌላኛው ጫፍም ቀስተደመናውንና መስታወት የሚመስለውን ንጹሕ ባሕርን አየሁ። "ማን ነው በዙፋኑ ላይ ያለው?" ብዬ ጌታን ጠየቅሁት። እርሱም: "አባቴ ነው፥ የሠራዊት ጌታ።" በማለት መለሰ። "አብን ማየት እችላለሁ?" ብዬ ነገርሁት። "አይ ሰዓቱ ገና አልደረሰም፥" በማለት ጌታ መለሰ።

አብን ባላየውም፥ በዙፋኑ ላይ የነበረው ኃያል ነበረ። ነጎድጓድና የመብረቅ ብልጭልጭታዎች ከዙፋኑ ሲወጡ አየሁ ውዳሴዎችንም ሰማሁ። "እነዚህን ውዳሴዎች ሰማሽ? እነዚህ ውዳሴዎች የተዋጁት ሰዎች ውዳሴዎች ናቸው።" በማለት ኢየሱስ ነገረኝ። ሰባት መላእክት አየሁ፥ እያንዳንዳቸው ወርቃማ ጎድጓዳ ሣህን ይዘዋል፤ ሰባት ሌሎች መላእክትም መለከት ይዘዋል። "ጌታ ሆይ፥ እነዚህ መላእክት እነማን ናቸው?"፥ ጌታም: "መላእክቱ የያዙት ሰባቱ ጎድጓዳ ሣህኖች በእግዚአብሔር ቁጣ ተሞልተዋል። በቅርቡ ይፈስሳሉ እና መለከቶቹ ሲነፉም ቤተክርስቲያኔ (እንደ አባቴ ፈቃድ የሚኖሩት እነዛ ክርስቲያኖች) ወደላይ ይነጠቃሉ። በታላቁ መከራ ጊዜ እነርሱ በምድር(በመሬት) ላይ አይሆኑም። የክርስቶስ ተቃዋሚ፥ የኃጢአት ሰው ራሱን

*ከመግለጡ በፊት፥ የእኔ ቤተክርስቲያን የመጨረሻውን መለከቶች ድምፅ ትሰማለች፥ እነርሱም(ቤተክርስቲያኔም) በአየር ላይ እኔን ይገናኙኛል።*" ([1ኛ ተሰሎንቄ 4:16]) በማለት መለሰ።



ውድ ጓደኛዬ ሆይ፥ ከታላቁ ዙፋን ፊት ለፊት እዚያ ነበርሁ፥ ምንም የሰዓት ግንዛቤም አልነበረኝም። የእርሱ ቤተ ክርስቲያን(እውነተኛ አማኞቹ) እንዴት ወደላይ እንደምትነጠቅ ኢየሱስ አሳየኝ! ሺሆች ሰዎች ሲጠፉ(ሲሰወሩ) በራእይ አየሁ። ይህ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ነው የሆነው፥ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የጠፉትን ዜና (ስለ ጠፉት) አስታወቁ። ጋዜጣዎች ደግሞ (በቀይ ቀለም በትልቁ አርእስተ-ዜናዎች) አድርገው ዜናውን አወጡ። ጌታ: "*ዜናው በቅርቡ ይሆናል። የአባቴ ፍርዶች በምድር ላይ እስካሁን ካልመጡ፥ እኔን የእውነት በሚያፈቅሩኝ ታማኝ በሆኑ ክርስቲያኖች ምክንያት ነው።*" በማለት ነገረኝ።



ከዛ በኋላ፥ የኃጢአትን ሰው መታየት አየሁ። እሱ ለምድር ነዋሪዎች "*እኔ ለእናንተ ሰላምና ደህንነት እያመጣሁላችሁ ነው*" እያለ ነበር፥ ከጥቂት ጊዜ በፊትም(አሁን) ሆኖ የነበረውን ሁኔታ ሰዎቹ ወዲያውኑ ረሱት። ኢየሱስ(ያሑሹዋ): "*በጥንቃቄ ተመልከቺ!* ።" ብሎ ነገረኝ። በራእዩ ውስጥ ሰባቱን ጓድጓዳ-ሣህኖች(ጽዋዎች) ይዘው ሰባቱን መላእክት አየሁ። ውድ ጓደኛዬ ሆይ፥ እየሆነ የነበረው ነገር ለማብራራት አስቸጋሪ ነው፤ መላእክቱ ሰባቱን የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች በምድር(በመሬት) ላይ ሲያፈስሱ አየሁ። መለከቶች መነፋት ጀመሩ። እግዚአብሔር ፍርዶቹን በምድር(በመሬት) ነዋሪዎች ላይ እያፈሰሰ ነበር፥ በሙሉ አገሮችም ጠፉ። ጌታ: "*ተመልከቺ! እነዚህ ሰዎች ሁሉ የቤተክርስቲያኔ አባል ነበሩ፥ አንዳንዶቹ ፓስተሮች ነበሩ።*" በማለት ነገረኝ። ይህን ሙሉ በሙሉ ስላልተረዳሁ "*እንዴት ነው በጣም ብዙዎቹ ሕዝብህ በታላቁ መከራ ውስጥ ሊሆኑ የቻሉት? እንዴት ነው ከእነርሱ መሐል ቃልህን የሰበኩ ፓስተሮች ሊኖሩ የቻሉት?*" በማለት ጌታን ጠየቅሁ። ኢየሱስ: "*አዎ፥ እነርሱ ቃሌን ሰብከዋል፥ ነገር ግን እነርሱ ከቃሌ ጋር ተስማምተው (በቃሌ መሠረት) አልኖሩም።*" በማለት መለሰ። ከዛ ጌታ ሌሎች ብዙ ፓስተሮችን እንዳይ ፈቀደልኝና እንዲህ ብሎ ነገረኝ: "*እነዛ ፓስተሮች ቃሌ እንደተጻፈው እንደዛው እየሰበኩ አልነበረም። ቃሌ ለእነርሱ ከፍለዘመን እንደማይስማማ አሰቡ። እነርሱ(እነዛ ፓስተሮች) የበለጠ እቃዎችን ስለሚወድዱ፥ በአስራት ብዙ ወደሚሰጡት እጅግ በየለጠ አድልዎ ነበራቸው (ብዙ አስራት ለሚሰጡት ለእነርሱ ያደሉ ነበር)። የጠራኋቸው እኔ እንደሆንሁ ሂጂና ለባሪያዎቼ ንገሪያቸው፥ ያ ብርና ወርቅም ለእኔ ይገባል(የእኔ ነው) እኔም እንዲታላቅነቴና እንደ ክብሬ ለእነርሱ እሰጣቸዋለሁ። ቃሌ እንደተጻፈው እንደዛው ቃሌን እንዲሰብኩት ንገሪያቸው። ለቃሌ ሌላ ትርጉም የሚሰጡት ብዙዎች ናቸው። ቃሌ የእኔ ቃል ነው፥ እናም ማንም ሊቀይረው አይችልም። እንደተጻፈው እንደዛው የግድ መሰበክ አለበት። ለራሳቸው ጥቅም ቃሌን የሚያዛቡ(የሚያጣምሙ) ብዙዎች ከሕዝቤ መሐል አሉ።*"

ከዛ በኋላ፥ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ውስጥ አንድ ቦታ ገባን ጌታም: “*የምታዪው ገነት ነው።*” አለኝ። ሐዋርያትን አየሁ እኔም ጌታን “*ጌታ ሆይ አብርሃም የት አለ?*” ብዬ ጠየቅሁት። አንድ ያረጀ ሰው ለማየት እየጠበቅሁ ነበር፥ ነገር ግን በድንገት 25 ዓመት የሚሆነው አንድ ወጣት ሰው እየቀረበን ሲመጣ አየሁ፥ ኢየሱስም “***ይህ የእምነት አባት አብርሃም ነው***” አለኝ።




እዚያ እንዳየኋቸሁ እንደ ሁሉም ሊነገር የማይችል ውበት ያላት አንድ በጣም ውብ ሴትን ጌታ ጠራ፥ እርሱም: “***ይህች ማርያም ናት! ሂጂና ማርያም የሰማይ ንግሥት እንዳልሆነች ለሁሉም ንገሪ። የሰማይ ንጉሥ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ እና የጌታዎች ጌታ እኔ ነኝ፤ እኔ ነኝ፡ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ያልኹት።*** ([ዮሐንስ 14: 6-7](ዮሐንስ 14: 6-7))። ***ዓይኑ ለተሸፈነ የሰው ዘር ምንም ፑርጋቶሪ እንደሌለ ሂጂና ተናገሪ፥ ቢኖርማ ኖሮ ባሳየሁሽ ነበር። በዚያ ፈንታ ያሳየሁሽ ሲኦል፥ የእሳት ባሕር፥ የከበረችው ኢየሩሳሌም፥ እና ገነት አለ። ነገር ግን ፑርጋቶሪ እንደሌለ ንገሪያቸው፤ ፑርጋቶሪ ከዲያብሎስ የሆነ ውሸት እንደሆነ ንገሪያቸው፥ ምንም ፑርጋቶሪ የለም።*** ” (ፑርጋቶሪ፥ ኃጢአተኞች ከሞቱ በኋላ ኃጢአታቸው እንዲሰረይ የሚፀፀቱበት/የሚሠቃዩበት ቦታ ነው ከዚያም ወደ ገነት ይሄዳሉ የሚል የዲያብሎስ(የሰይጣን) ውሸት ነው!።)

ከዛ ጌታ ወደ ዘውዶች ግምጃ ቤት መራኝ። “***እኚህ የሕይወት ዘውዶች ናቸው... ምን ታዪአለሽ?***” አጥቢያ ቤተክርስቲያኔን፣ የዚያ ማሕበረሰብ አማኞች ሲዘምሩና ሲሰብኩ አየሁ፥ ከዚያ ኢየሱስን: “*የአጥቢያ ቤተክርስቲያኔ የማሕበረሰቤ አማኞች ስሞች ለምንድን ነው በዚህ መጽሐፍ ላይ ያልተጻፈው?*” በማለት ጠየቅሁት። እርሱም: “***ምድር ላይ በሚያደርጉት የተሳሳተ(መጥፎ) ተግባር(ድርጊት) ምክንያት ነው።***” (**[ራእይ 3:11](ራእይ 3:11)**) ብሎ ነገረኝ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ተመልሼ ምድር(መሬት) ላይ እንድመጣ፣ ተመልሼ ሥጋዬ(አካሌ) ውስጥ እንድገባ ጌታ ፈቀደልኝ፥ ጉዞውም ተጠናቀቀ።

## ሁለተኛ ጉዞዬ

አንድ ቀን ሁላችንም በጸሎት ስብሰባ ላይ ነበርን፥ በቁጥርም ወደ ሀያዎች እንሆናለን። እንደተለመደው፥ ጌታን በማወደስና በማምለክ ጀመርን።



በድንገት የእግዚአብሔር መገኘት ተሰማን። ልክ የጴንጤቆስት (የባዕለ ሀምሳ፥ የሻቩዖት) ቀን እንደነበረው እጅግ ኃይለኛ ነበር። የባሌን እናት አስታወስሁ፥ አረጋዊና በጣም አፍቃሪ(ታማኝ) ሴት፥ “*በርናርዳ፥ በውዳሴ ጊዜ ድምፁን ዝቅ እናድርገው፥ በጣም የበዛ ድምፅ እያሰማን ነው*” ብላ ነግራኛለች። ውዳሴው እንደ ፏፏቴ ድምፅ ስለነበረ እርሷ ትክክል ነበረች። ድምፁን እንዲቀንሱት ወንድሞቼን ልጠይቅ ሳለሁ፥ ጌታ: “***አንዳች አትበዪ! በዓለም፥ ሰዎች ድምፅ ሲያበዙ ማንም ግድ አይለውም፥ ታዲያ ለምንድን ነው አንቺ ውዳሴውን የምታስቆሚው?***” እያለ ሲነግረኝ ሰማሁ።

ስለዚህ ጌታን ማወደሳችንንና ማምለካችንን ቀጠልን። የሆነ ትልቅ ነገር እንደሚሆን ተሰማኝ። በመጀመሪያ ጉዞዬ ጊዜ ጌታ የነገረኝን ወዲያውኑ አስታወስሁ: “***ተመልሼ እመጣልሻለሁ*** ።”

በድንገት ደማቅ ብሩህ ብርሃን ቤቴን ሲያጥለቀልቀው አየሁ። ወንድሞቼም ብርሃኑ መጥቶ ሲታይ አይተዋል። እነርሱ ሁሉም **በእግዚአብሔር ፊት** በጉልበታቸው ተንበረከኩ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅሁም፥ እኔም ጸንቼ ቆምሁ። ያ ብርሃን የበለጠ እየደመቀ መጣ፥ የሰውንም ቅርጽ ያዘ። ከፊት ለፊቴ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ**፥ እጅግ ውብ እና በፍቅር የተሞላ። በምድር ላይ፥ በወንድ ፊት ላይ እንዲህ ዓይነት ውበት በፍጹም አይቼ አላውቅም። **እርሱ** ወደ እያንዳንዶቹ ወንድሞቼ ቀረበ። **ጌታ** ለእኔ እንደመጣ ለወንድሞቼ ልነግር ሳለሁ ግን በልሳኖች መናገር ጀመርሁ። (**1ኛ ቆሮንቶስ 14:39-40**)

**ኢየሱስ** ልክ እኔን ሲመለከት፥ መንፈሴ አካሌን ትታ ወጣች እኔም በአየር ላይ ነበርሁ። **ኢየሱስ** እጆቼን ያዘና ወደ ዶሚኒካን ሪፐብሊክ ሄድን። ከተማዋ ስንደርስ፥ **ጌታ**: "***በአባቴ ፊት ይህች አገር የፈጸመችው ሁለት ትልልቅ ኃጢአቶች አሉ፥ ጥንቆላ እና ጣዖት አምልኮ።***" በማለት ነገረኝ። የዚያች አገር ሰዎች ከአስማተኞችና ከጣዖት ኋላ ሲሮጡ አየሁ።



ከዛ በኋላ፥ **ጌታ** ወደ ቬንዝዌላ አመጣኝ ከዚያም ወደ ሜክሲኮ። በቬንዝዌላ፥ ከ**ኢየሱስ** ጋር በአየር ላይ ነበርሁ፥ ነገር ግን ሰዎቹ ወደ ማጂክ(መተት፥ አስማት)፣ ወደ ጥንቆላ፣ እና ወደ ጣዖት አምልኮ ሲዞሩ አየሁ። በሜክሲኮ፥ ሰዎች አጋንንትን ሲገናኙና አጋንንትን ሲያመልኩ አየሁ። **ጌታ**: "***የዚህ ኃጢአት ትላቅ አሰቃቂነት አባቴ ጋር ደርሶአል። የአገሪቷ ነዋሪዎች ንስሐ ገብተው ወደ እኔ ካልተመለሱ እንደማስጠንቀቂያ የምሰጠው የመጀመሪያ ምልክት የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል(ይኖራል)።***" በማለት ነገረኝ።

*(በኋላ ላይ ወደ ምድር(መሬት) ስመለስ፥ ወደ ሜክሲኮ ሄድሁ ይህንንም መልእክት ሰበክሁ። ሰዎቹ አላዳመጡም እና በቅርቡ አስከፊ የመሬት መንቀጥቀጥ በሜክሲኮ ነበረ)*

በአየር ላይ ሳለን፥ የ**አባቱ እጆች** በምድር ነዋሪዎች ላይ እንደተዘረጉ **ጌታ** ነገረኝ። ባሕር ጭራቅ የሚመስሉ በጣም ታላላቅ ሞገዶች ይዞ አየሁ። ማዕበል አውሎ ነፋሶች በምድር ላይ ሲሆኑ አየሁ። **ጌታ**ን: "*ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ ሲሆን ክርስቲያኖች ላይ ምን ይሆናል?*" በማለት ጠየቅሁት። እርሱም: "***ለእኔ ታማኝ ለሆኑት ለእነዚያ፥ ከጸጉራቸው አንዳችም እንደማይነካ ሂጂና ንገሪያቸው***" በማለት መለሰ።



ከዛ በኋላ **ጌታ** ወደ ሌላ ቦታ አመጣኝ፥ መሬት ተከፍሎ(ተሰንጥቆ) የነበረበትን ቦታዎች አየሁ። **ጌታ**: "***ብዙ አገሮች በቅርቡ ይወድማሉ(ይጠፋሉ)።***" በማለት ነገረኝ።

ከዛ ያን ቦታ ተውንና ውኃዎች በእንቅስቃሴ ላይ ሆነው ወዳየሁበት ወደ ሌላ ቦታ ሄድን። በመሿለኪያ ዋሻ ውስጥ ወደ ታች ሄድንና ወደ መሬት ጥልቆች ደረስን። ታላላቅ በሮች አየሁ። በመጀመሪያ ጉዞዬ ጊዜ እንዳየኋቸው ዓይነቶች አይደሉም። በእነዚህ በሮች ላይ ትልልቅ ሰንሰለቶች ነበሩ። **ጌታ** ወደ በሮቹ ሄደ፥ ሰንሰለቶቹን አስወገደ፥ በመሿለኪያው ውስጥም መራኝ።

ሺሆች ሰዎች ራሳቸው ዝቅ ብሎ፣ የተቀዳደደ ልብስ ለብሰው አየሁ። በላያቸው ላይ ትላልቅ ሰንሰለቶች ነበሩባቸው። ከዚያ እኔ: "*ጌታ ሆይ፥ ይህ ምን ማለት ነው?*" አልሁ። **እርሱ**: "***እነዚህ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ወደ ሲኦል እየሄዱ ነው።***" በማለት መለሰ። ከእነርሱ መሐል፥ የባሌን ታላቅ ወንድም አዶልፎን አየሁ። እርሱ አስቸጋሪ ሰው ነበረ፥ በፈለገ ጊዜ ሚስት ያገባና ይፈታ ነበር፥ እርሱም **እግዚአብሔር**ን ይረግም ነበር። ከዚያም ወደ ምድር ተመልሼ ሄጄ አዶልፎን ወደ ሲኦል ሊሄድ እንደሆነ እንዳስጠነቅቀው እንዲፈቅድልኝ **ጌታ**ን መለመን ጀመርሁ፥ **ጌታ** ግን አልመለሰልኝም። በድጋሜ አዶልፎንና ሚስቱን

በመሿለኪያው ውስጥ ሲሄዱ አየሁ። እነርሱ በሲኦል ጫፍ ላይ ነበሩ። ወደ ምድር(መሬት) ተመልሼ ሄጄ ያየኹትን ለሰዎች እንድነግር እንዲፈቅድልኝ ጌታን በድጋሜ ለመንሁት። ጌታ እጆቹን ወደ ላይ አነሣና: “*ሰዓቱ ሊያልቅ ጥቂት እንደቀረው (nearly over) ሂጂና ንገሪያቸው... ሺሆችና ሺሆች ሰዎች ወደ ሲኦል ይሆዳሉ፥ የአዶልፎ ሰዓት አልቆአል፥ እርሱ ሊሞት ነው።* ”


(ወደ መሬት ተመልሼ ስመጣ፥ በሕግ ወንድሜ የሆነው አዶልፎ የህይወት(የአኗኗር) መንገዱን መቀየር አልፈለገም። አንድ ቀን፥ ከሥራ በቶሎ ወደ ቤት መጣና ለሚስቱ: “*ከዚህ በኋላ መሥራት አልችልም፥ ልሞት እንደሆነ አንድ ነገር እየነገረኝ ነው።*” ሚስቱም: “*እንደተለመደው ስለሰከርህ ነው እንዲህ እያልክ ያለኸው።*” በማለት መለሰች። ሁለቱም ወደ አልጋ ሄዱ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፥ አንድ ራእይ አየች(ነበራት)። በራእዩ ባሏና ራሷ ቡትቶ ልብሶ ለብሰው በመሿለኪያ ውስጥ ሆነው ወደ ሲኦል እየሄዱ አየች። ጌታ: “*ለሁለታችሁም ሰዓት አልቆአል።*” ብሎ ሲነግራት ሰማች።)

አየር ላይ ሆኜ ሳለሁ ጌታ: “*ለሁለተኛ ጊዜ እዚህ ለምን እንዳመጣሁሽ ታውቂያለሽ? በመጀመሪያው ጉብኝትሽ ጊዜ፥ ጠፍተው የነበሩት የነፍሳት ቁጥር በአሁን ጊዜ ጠፍተው ካሉት እንደሚያንስ ላሳይሽ ነበር።*” በማለት ነገረኝ። በፊት ከጠፉት ይልቅ አሁን የጠፉ ብዙ ነፍሳት አሉ።

ከዛ፥ ኢየሱስ እና እኔ ያን ቦታ ተውንና በሁለተኛው ሰማይ ውስጥ ወደ ላይ ሄድን። የእግዚአብሔር መንግሥት፥ ሦስተኛው ሰማይ ስንደርስ፥ መላእክት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ጉድጉድ (ሽር ጉድ) ሲሉ አየሁ፤ ከዚያ ጌታን: “*ለምንድን ነው እነዚህ መላእክት በእንቅስቃሴ ያሉት?* ” በማለት ጠየቅሁት። ኢየሱስ(ያሑሹዋ): “*መላእክቴ እዚህ በእንቅስቃሴ መሆናቸው እውነት ነው፥ ነገር ግን መሬትም ደግሞ እንዴት በእንቅስቃሴ እንደሆነች ላሳይሽ ነው። ተጠንቀቂ፥ ምክንያቱም ብዙ አጋንንት መሬትን ወረዋታል። ዲያብሎስ ጥቂት ሰዓት ስለቀረው በክርስቲያኖች ላይ እጅግ ተናድዶአል።* ” በማለት መለሰ።



በጣም በኃይለኛ(በመጥፎ) ንዴት ሆነው አጋንንትን እንዳይ ጌታ ፈቀደልኝ፥ እና እርሱ ይህን ነገረኝ: “*የምታዪአቸው እነዚያ አጋንንት የዝሙት አጋንንት ናቸው። እነሱ ሺሆች አገልጋዮቼን(ባሪያዎቼን) ያጠቃሉ እና ብዙዎች እዛ ኃጢአት ውስጥ ይወድቃሉ። ዲያብሎስ አገልጋዮቼን እንዲወድቁ በማድረግ ለምን እንደሚሳካለት ታውቂአለሽ? ምክንያቱ አገልጋዮቼ ለእኔ ሁሉንም ክብር ስለማይሰጡኝ ነው። እነርሱ(የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች) ክብሬን ይሰርቁና ኩሩ ይሆናሉ። በዚያ ላይ፥ ሚስቶቻቸው በታላቅ መንፈሳዊ ረብሻ(ትርምስምስ) ውስጥ ይኖራሉ። እነርሱ(ሚስቶቻቸው) ቤታቸውን በጥበብ አልገነቡም።* ” (**1ኛ ጢሞቴዎስ 2:11-14**)



ልቆጥራቸው የማልችላቸው ሺሆች መላእክትን አየሁ፥ ለውጊያ(ለጦርነት) የተዘጋጁ ብዙዎቻቸው ነበሩ። ከዛ ኢየሱስ “*ሕዝቤን ለመጠበቅ እነዚህን ሺሆች መላእክት አሁን በምድር ላይ እየላክሁ ነው። በእነዚህ የመጨረሻ ቀናቶች፥ ጥበቃው እጥፍ ይሆናል። ሰይጣን ደግሞ ጥቃቶቹን እጥፍ ያደርጋል፥ ነገር ግን አምላካችሁ ታላቅና ኃያል እንደሆነ መርሳት የለባችሁም። እናንተ ከእርሱ(ከአምላካችሁ) ጋር ብትጣበቁ እናንተ ላይ ምንም አይሆንም።* ” በማለት ነገረኝ።

## ግብዣው

ጌታ ከዛ ወደ ሌላ ቦታ አመጣኝ። አንድ ግዙፍ ጠረጴዛ ዙሪያውን በወርቃማ ወንበሮች ተከብቦ አየሁ። በእያንዳንዱ ወንበር ላይ፥ አንድ ስም ተጽፎበታል፥ ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ንጹሕ ልብስም ደግሞ ተቀምጦበታል። ከእያንዳንዱ ወንበር ፊት ለፊት፥ በጠረጴዛው ላይ ዘውዶችን አየሁ። ከዛ ከሌሎቹ የተለቀ አንድ ወንበር እንዳለ ልብ አልሁ። ከዚያ ወንበር ፊት ለፊት አንድ ግዙፍ ጽዋ በወርቅ ነበረ። ሄጄ ጽዋው ውስጥ ምን እንዳለ እንዳይ አየሱስ ነገረኝ። ጽዋው ሊቀርብ የተዘጋጀ በወይን የተሞላ ነበረ። ኢየሱስ: "*ወይኑ ሊቀርብ ለምን ዝግጁ እንደሆነ ታውቂያለሽ? እኔ በሩ እንደሆንሁ፥ እኔ በቅርቡ እንደምመጣ ሂጂና ለሕዝቤ ንገሪ።*" በማለት ነገረኝ።

ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስና አንድ ዘውድ ጌታ ሰጠኝ። ልብሱን ለበስሁ ዘውዱንም አደረግሁና የሆነ የመስታወት ዓይነት ወዳለበት ወደ አንድ ቦታ ሄድሁ። ኢየሱስ: "*በልብሰሽ ላይ ጉድፍም(እንከንም) ሆነ መጨማደድ የለም፥ አይደለም እንዴ? እንደዚህ እስካለበሰ ድረስ፥ ማንም በዚህ በርም አይገባም በዚህም ጠረጴዛ ላይ ቦታ አይወስድም። በምድር ላይ ከሕዝቤ መሐከል አንዳንዶች ልብሳቸውን አቆሽሸዋል። ሌሎች የተጨማደዱ ልብሶች አሏቸው፥ አሁንም ሌሎች የራሳቸውን አስቀምጠዋል፥ ረስተዋቸዋልም (ልብሶቻቸውን)። ልብሳቸውን የሚያጥቡበት፣ ልብሳቸውን የሚተኩሱበት እና ልብሳቸውን መልሰው የሚወስዱበት ሰዓት አሁን እንደሆነ ለሕዝቤ ንገሪ። ልብሳቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳቸው ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ አለባቸው፥ ምክንያቱም ንጉሡ በአባቱ መንግሥት የሰርጉን እራት ግብዣ በቅርቡ ያከብራል።*" ([ማቴዎስ 22:1-14]) ብሎ ነገረኝ።

## ቤተሰቦቼ

ከተፋቱ ወላጆች ነው እኔ የመጣሁት እኔም ከአባቴ ጋር ነው ያደግሁት። እናቴ በጣም ሃይማኖታዊ ሴት ነበረች። አባቴ ግን በምንም አያምንም። በካቶሊክ ቃል ኪዳን ውስጥ ያለች አንድ እህት አለችኝ፥ እኔ ግን ኢየሱስ በቅርቡ ከዚያ እንደሚያወጣት አውቃለሁ እና እርሷም ከእኔ ጋር ወንጌልን ትሰብካለች። ለእርሷ ብዙ እጸልያለሁ። በዚያ ረቂቅ (mystic) ሀይማኖት ውስጥ የእናቴን ህይወት ሳስብ፥ በገነት የመጀመሪያው ጉዞዬ ጊዜ በጌታ ፊት አለቀስሁና: "*ጌታ ሆይ እናቴ ጠፍታለች፥ ሆኖም ወንጌልን ለእርሷ ሰብኬላታለሁ፥ እርሷ ግን ማዳመጥ አልፈለገችም። የበለጠና የበለጠ እርሷ ወደዚያ አረማዊ ሃይማኖት ተጣብቃለች።*" ብዬ ነገርሁት። ጌታም: "*እኔ እናትሽን አድናታለሁ፥ ነገር ግን እኔ ወዲያው እቤት እወስዳታለሁ ያለበለዚያ ተመልሳ ኃጢአት ውስጥ ትወድቅና ወደ ሲኦል ትሄዳለች። በዚህ ምክንያት፥ እርሷ እንደተለወጠች፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትሞታለች እዚህም ገነት ውስጥ ትመጣለች።*" በማለት መለሰ።

መሬት(ምድር) ላይ ተመልሼ ስመጣ፥ የሰጠኝን የተስፋ ቃል ጌታን እያስታወስኩት ጸለይሁ፣ አለቀስሁ፣ አቃሰትሁ፥ ነገር ግን የበለጠና የበለጠ በሃይማኖቷ ጣዖት አምልኮ ውስጥ ተሳትፋ የነበረችውን እናቴን አየኋት። አንድ ቀን እግዚአብሔር እናቴን ለመለወጥ ወንድ ልጄን ተጠቀመ። ከተለወጠች ልክ ከሦስት ቀኖች በኋላ ሞተች!



በገነት ሁለተኛ ጉዞዬ ጊዜ ጌታ: "*ተመልከቺ፥ አፌ የሚለውን፥ እጆቼ ፈጸሙት።*" በማለት ነገረኝ። እናቴን በዚያ ውብ ገነት ውስጥ አየኋት፤ ከሌሎች ሴቶች መሐከል ነበረች። ሺሆች ሕፃናት ነጭ ተላብሰው ጌታን እያወደሱና እያከበሩ ወዳየሁበት ወደ አንድ ቦታ ሄድን። ኢየሱስ: "*እኚህ ሕፃናት <u>በወላጆችና በወንጀለኛ ዶክተሮች ወርደው(ጨንግፈው)</u> የነበሩት ናቸው። ገና በእናታቸው ማኅፀን ውስጥ ሳሉ ሰዎች የገደሏቸው ሕፃናት፣ እና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ኮንቴይነር(በርሜል)ና በወንዞች ውስጥ የተገኙ ሕፃናት እዚህ በሰማይ ናቸው።*" ብሎ ነገረኝ።

ውድ ወንድሞችና እህቶች፥ ልታስቡት በምትችሉት በተቃራኒው፥ ፅንስ ከመፀነሱ(ከእርግዝናው) ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ለጌታ ሰው ነው።

ኢየሱስ : "*በርናርዳ፥ እኔ ብርታትሽ(ጥንካሬሽ) ነኝና ሥሪ። ይህ መልእክት በዓለም ሁሉ ውስጥ መቅረብ(መታተም) አለበት። ለክርስቲያኖች፣ ለፓስተሮች(ለእረኞች)፣ እና አንቺን ጨምሮ ለሁሉም የምድር ነዋሪዎች የሆነ መልእክት ነው። ቅዱስ የሆነ ቅዱስ መሆኑን ይቀጥል።*" በማለት በድጋሚ ነገረኝ።

በዚያ ቅጽበት የሰማይ ደጆች ተከፍተው ነበር። አንድ ውብ ተንቀሳቃሽ ደረጃ ነበረ። ኢየሱስ ሺሆች መላእክት እንዲመጡ ጠራቸው፥ ከዚያም ጌታ ወደ ቤት አጅቦ መለሰኝ።

እቤት ስንደርስ፥ መንፈሴ ተመልሶ እስኪመጣ እየጠበቁ ባለቤቴንና ክርስቲያን ወንድሞችን አየኋቸው። ሥጋዊ አካሌን አየሁት፥ እኔም ጌታን ይህን አካል ከእንግዲህ እንደማልፈልገው ነገርኩት። ጌታም: "*ሰዓትሽ አሁን አይደለምና፥ ተመልሰሽ ከእኔ ጋር ወደ ሰማይ መሄድ አትችዪም። እነርሱ ይዘጋጁ ዘንድ (እንዲዘጋጁ)፥ ያየሽውን መጀመሪያ ለሕዝቤ መንገር አለብሽ።*" በማለት ነገረኝ። በኃይለኛ ድምፅ እርሱ: "*ግቡ እና ሕይወት ተቀበሉ፥ እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ፥ በእኔ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል (ይኖራል)*" ([**ዮሐንስ 11: 25-26**]) በማለት ነገረኝ።

**ምስክርነቱ ተፈጸመ**

**ክብር ለእሥራኤል አምላክ ለሠራዊት ጌታ፥ ለእሥራኤል ኃያል ለእሥራኤል ንጉሥ፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለቅዱስ እግዚአብሔር አብ ለቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይሁን።**

**ክብር በቀራንዮ ላይ በመስቀል ተሠቅሎ፣ ሞቶ፣ ተቀብሮ፣ ከሞትም በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ላዳነን፥ በደሙም ከኃጢአታችን ላጠበን፣ ለአባቱም መንግሥት ካሕናትና ነገሥታት ላደረገን፥ ላዳነን፥ በቅድስናና በጽድቅ ላፈቀረን፥ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ለሆነው፥ ጌታችንና ቤዛችን ሕይወታችንና አዳኛችን ንጉሣችንና መንገዳችን እውነትና ብርሃን ለሆነ ለቅዱስ እግዚአብሔር አብ ልጅ ለቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋናና በረከት ጥበብና ኃይል ክብርና ውዳሴ ማዳንም ይሁን። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ስምህ ይባረክ፥ አሜን ሃሌ ሉያ፥ ማራናታ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና።**

ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረኀመው። **ሃሌ ሉያ**

Translations and MP3 also available

የዋናው ምስክርነት አካል ያልነበሩ የስዕል ማብራሪያዎች

በኋላ ላይ ተጨምረዋል።
www.DivineRevelations.info/BERNADA